# የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎች፤ ጠቅላላ ጉባዔ

**General Assembly of Kinijit's North America Supporters**

Date - August 21, 2006

# የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎች፤ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ከ25 ልዩ ልዩ የአሜሪካ ክፍለ ግዛቶች የተገኙ የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎች፤ ኦገስት 19 እና 20፣ 2006 ዓ.ም ከቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ጋር በስፋትና በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥተዋል።

1- በእስር የሚገኙ የቅንጅት መሪዎችን ጉዳይ በማስቀደም በውጭ አገር የሚደረገውን የዲፕሎማሲ ትግል እና እርዳታ ይቀጥላል።

2- በቅንጅት አለም አቀፍ እና በድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ስላለው ግንኙነት፤ እንደዚሁም የአለም አቀፉን አመራር ተጠሪነት፣ የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አደረጃጀትና ሌሎችም በርካታ ነጥቦች ተነስተው ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ክርክሮች፣ ውይይቶችና መስማማቶች ላይ ተደርሷል። ገንቢ ሃሳቦችም ወደ ስራ የሚተረጎሙበትን፣ ጥያቄዎችም በሂደት መልስ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ አመቻችቷል።

3- የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ትግሉን በስፋት ለማራመድ ያስችለው ዘንድ ለሚደረገው እንቅስቃሴ አስፈላጊውን በጀት የሰሜን አሜሪካ አመራር ይመድባል፤ የፋይናንስ ድጋፍ ያደርጋል።

4- ጉባዔው የአስተዳደርን እና የፋይናንስን ጉዳይ በተመለከተ የተሟላ ጥናትና ሪፖርት በ60 ቀናት ውስጥ የሚያቀርብ ሰባት አባላት የሚገኙበት ኮሚሽን አቋቁሟል። በተለይም በፋይናንሱ በኩል ከቀድሞ የድርጅቱ ኦዲተር የቀረበለትን የቃል አስተያየት አድምጧል፤ ውይይትም አድርጓል። ተጨማሪ ህጋዊ የሆነ እና ጥልቀት ያለው ሪፖርት እንዲያቀርብ ለኮሚሽኑ ሃላፊነት ተሰጥቶታል።

5- በሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎች ስር ይተዳደር የነበረው የቅንጅት ድረ ገፅ፤ አስተዳደሩ በቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ስር እንዲሆን ተወስኗል።

6- በአጠቃላይ ጉባዔው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ በውጭ ሃገራት የሚገኙትን ሃገር ወዳዶች፤ ለትግሉ የሚያደርጉትን አስተዋጽዋኦ በከፍተኛ አድናቆት የሚመለከተውና ይኸው ድጋፍ ወደፊትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርቧል። ይኸንንም የህዝብ ፍላጎትና ድጋፍ በአግባቡ በመጠቀም የጎደለውንም አሟልቶ ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድነት ለመስራት ቃል ኪዳን በመግባት ስብሰባው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

የቅንጅትን መንፈስ አንግበን እንነሳ!
የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል!
የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪዎች ጠቅላላ ጉባዔ
አርሊንግተን፣ ቨርጂኒያ (ኦገስት 2006)